# *በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የየካ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የ6ኛ ክፍል አካባቢ ሳይንስ ሞዴል ፈተና*

*2015ዓ.ም 2023እ.ኤ.አ*

*የፈተናው ሰዓት - 1ሰዓት*

*አጠቃላይ ትዕዛዝ*

በዚህ **የአካባቢ *ሳይንስ*** ፈተና ውስጥ 40 ጥያቄዎች ተካተዋል፤ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛው መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል በፈተና ላይ የተሰጡትን ትዕዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተና ውን መስራት ይጠበቅባችኋል። መልሱን የምትመልሱት በተዘጋጀዉ በመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው። በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ የሚጠቆረው በዕርሳስ ብቻ ነው ፤ ትክክለኛው መልስ በማጥቆር ሲሰራ የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጠቆር አለበት፤የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በሚገባ በመጥፋት መፅዳት አለበት። ፈተናውን ሠርቶ ለመጨረስ የተፈቀደው ሰዓት 1 ሰዓት ነው።ፈተናውን ሠርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን ማጥቆሪያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናውን መስራት ማቆም አለብን። ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ(ኟ)እስከሚነገር ድረስ በቦታችሁ በመቀመጥ መጠበቅ አለባችሁ።መኮረጅ ወይም በፈተና ሰዓት የፈተናውን ሕግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ እንዳይፈተን ይደረጋል። ፈተናውን መስራት ከመጀመራችሁ በፊት መልስ በመስጫው ላይ መሞላት ሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት።

***ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም!***

1. ከሚከተሉት ውስጥ የምስራቅ አፍሪካን ፍፁማዊ መገኛን የሚገልፀው የትኛው ነው?

ሀ. ከ87$^0$ ሰሜን እስከ 27 ምስራቅ ኬክሮስ እንዲሁም 22$^0$ ምዕራብ እስከ 51$^0$,28' ምስራቅ ኬንትሮስ ነው

ለ. ከ18$^0$ ሰሜን እስከ 27$^0$ ደቡብ ኬክሮስ እንዲሁም 22 ምስራቅ እስከ 51$^0$,28' ምስራቅ ኬንትሮስ ነው

ሐ. ከ90 ሰሜን ምስራቅ እስከ 29$^0$ ደቡብ ኬክሮስ እንዲሁም 31$^0$ 29 ምስራቅ

መ. ከ150$^0$ ሰሜን እስከ 29$^0$ ደቡብ በኬንትሮስ

2. በካርታ ላይ ወይም በሉል ላይ ከሰሜን ወደ ደቡብ ወይም ከደቡብ ወደ ሰሜን የሚሰመሩ የሃሳብ መስመሮች አጠቃላ ብዛታቸው ስንት ነው?

| | |
|---|---|
| ሀ. 180 | ሐ.360 |
| ለ.90 | መ. 366 |

3. ከሚከተሉት ውስጥ የታላላቅ ሐይቆች ክልል ሀገር ***የሆነው*** የቱ ነው?

| | |
|---|---|
| ሀ. ኢትዮጵያ | ሐ. ኮሞሮስ |
| ለ. ኬኒያ | መ.ጁቡቲ |

4. ከሚከተሉት ውስጥ በኡጋንዳ ኮንጎ ድንበር ላይ የሚገኘው ተራራ የተኛው ነው?

| | |
|---|---|
| ሀ.ሩዋንዞሪ | ሐ. ኪሊማንጃሮ |
| ለ. ሜሩ ተራራ | መ. ኤልጎን |

5. ከሚከተሉት ውስጥ ምስራቅ አፍሪካን ***የማያዋስነው*** ውሃማ አካል የሆነው የቱ ነው?

| | |
|---|---|
| ሀ. ቀይባህር | ሐ. የአባይወንዝ |
| ለ. የኤደን ባህር ሰላጤ | መ. የህንድ ውቅያኖስ |

6. የምስራቅ  አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ በአፍሪካ ብቻ የሚሸፍነው ስንት ኪ.ሜ ነው?

| | |
|---|---|
| ሀ. 5600 | ሐ.8300 |
| ለ. 7200 | መ. 7300 |

7. ሩቅ ያሉ ቦታዎችን ለማየትና ለመመርመር ስለተለያዩ በሽታዎች ለመከሰት ትንበያ ለመስጠት የምንጠቀምበት መተግበሪያ የትኛው ነው?

| | |
|---|---|
| ሀ.  ጎግል ካርታ | ሐ. ጂፒኤስ |
| ለ. ጎግል ኧርዝ | መ. ማይክሮ ሶፍት |

8. ኦክስጂንንና አልሚ ምግቦችን ለሰውነታችን ህዋሶች የሚሰራጩበት እንዲሁም ካርቦንዳይ ኦክሣይድ እና ሌሎች ቆሻሻዎች በደም አማካኝነት የሚሄዱበት ሂደት ምን ይባላል?

| | |
|---|---|
| ሀ. የደም ዑደት | ሐ. ትንፈሣ |
| ለ. ደም | መ. የምግብ መፈጨት |

9. ሰውነታችን ሲዳማ ብዙ ደም እዳይፈስን ለማርጋት የሚጠቅመን የትኛው የደም ክፍል ነው?

ሀ. ፕሌትሌት | ሐ. ቀይ የደም ህዋስ

ለ. ነጭ የደም ህዋስ | መ. ፕላዝማ

10. ለሰውነታችን ህዋስ በጣም ቅርብ የሆኑት የደም ስሮች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ደም መልስ | ሐ. አርተሪ

ለ. ደም ቅዳ | መ. ቀጫችን የደም ስሮች

11. ከቀኝ ተቀባይ ልበ ገንዳ የተቀበለውን ደም በፑልሞናሪ አርተሪ ወደ ሳንባ የሚረጨው የልብ ክፍል የትኛው ነው?

ሀ. ግራ አቀባይ ልበ ገንዳ | ሐ. ቀኝ ተቀባይ ልበ ገንዳ

ለ. ግራ ተቀባይ ልበ ገንዳ | መ. ቀኝ አቀባይ ልበ ገንዳ

12. በኮረዳነት ወቅት በሴቶች ላይ ***የማይታየው*** ስነ ህይወታዊ ለውጥ የትኛው ነው?

ሀ. የድምፅ መቅጠን | ሐ. የደምፅ መጎርነን

ለ. የጡት ማጎጥጎጥ | መ. የዳሌ መስፋት

13. የስርዓተ ትንፈሳ ጠቀሜታ ***ያልሆነው*** የቱ ነው?

ሀ. ካርቦንዳይኦክሳይድ ለህብረህዋስቻችን ማሰራጨት

ለ. ለማውራት

ሐ. በሰውነታችን ውስጥ የሙቀትና ቅዝቃዜን ተመጣጣኝ ለማድረግ

መ. ለማሽተት

14. የስርዓተ ትንፈሳን በቅደም ተከተል ሲቀመጥ ትክክል ***የሆነው*** የትኛው ነው?

ሀ. ተገንጣይ የአየር ቧንቧ ⇒ደቂቅ ትንቧ ⇒የአፍንጫ ቀዳዳ ⇒ ሰርን ⇒ ድህረአፍ⇒አብይ የአየር ቧንቧ ⇒ የአየር ከረጢት

ለ. የአፍንጫ ቀዳዳ ⇒ደቂቅ ትንቧ ⇒ሰርን ⇒ ድህረ አፍ ⇒ አብይ የአየር ቧንቧ⇒ተገንጣይ የአየር ቧንቧ⇒ የአየር ከረጢት

ሐ. የአፍንጫ ቀዳዳ ⇒ ሰርን⇒ ድህረ አፍ ⇒ አብይ የአየር ቧንቧ⇒ተገንጣይ የአየር ቧንቧ⇒ደቂቅ ትንቧ ⇒ የአየር ከረጢት

መ. የአፍንጫ ቀዳዳ ⇒ ሰርን⇒ አብይ የአየር ቧንቧ⇒ተገንጣይ የአየር ቧንቧ⇒ድህረ አፍ ⇒ የአየር ከረጢት

15. በሀገራችን ኢትዮጵያ ቡናን የማስከን ሒደት የምናከናውንበተ የድብልቅ መለያ ዘዴ የቱ ነው?

ሀ ጥለያ | ሐ. ትነት

ለ.ንጥረት | መ. ቀረራ

16. የዘይትና የውሃ ድብልቅ በየትኛው አይነት መለያ ዘዴ በቀላሉ ይለያል?

ሀ. ጥሊያ ሐ. በቀረራ

ለ. በንጥረት መ. በትነት

17. በኢምጋት ጊዜ የኦክስጅን መጠን ስንት ነው?

ሀ. 0.3% ሐ. 21%

ለ.16% መ. 17%

18.የልብ ምትን የምናዳምጥበት መሳሪያ ምን ይባላል?

ሀ. ማይክሮሶፍት ሐ. ቴሌስኮፕ

ለ. ስቴቶስኮፕ መ. ማይክሮስኮፕ

19.እንቁላል ከእንቁልጢ መውጣትና ወደ ማህፀን ቦይ መግባቱን ተከትሎ የሚመጣ ስነ ህይወታዊ ለውጥ ምን ይባላል?

ሀ. የጡት ማጎጥጎጥ ሐ. የወር አበባ መታየት

ለ. የድምፅ መጎርነን መ. የዳሌ መስፋት

20. በኢትዮጲያ ከሚገኙ ወንዞች መካከል በሶማሊያ አሸዋ ውስጥ ሰምጦ የሚቀረው ወንዝ የትኛው ነው?

ሀ. ገናሌ ሐ. ዋቢ ሸበሌ

ለ. አባይ መ. አዋሽ

21.ከእርሻና ከከብት እርባታ ጎን ለጎን ዛፎችን መትከልና መንከባከብ ምን ይባላል?

ሀ. አፈራርቆ ማረስ ሐ. ድነና

ለ. ጣምራ የደን እርሻ መ. ዳግም ድነና

22.ከኢትዮጲያ ከወጣ በኋላ ጁባ በመባል የሚታወቀው ወንዝ የቱ ነው?

ሀ. የዛምቢዚ ወንዝ ሐ. የዋቢ ሸበሌ ወንዝ

ለ. የአዋሽ ወንዝ መ. የገናሌ ወንዝ

23.የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታ ልዩነታቸው ምንድን ነው?

ሀ. የጊዜ ርዝመት ሐ. በመጠናቸው

ለ. በይዘታቸው መ. በግዝፈታቸወ

24.ወደ ሜዲትራኒያን ባህር የሚገባው ወንዝ የትኛው ነው?

ሀ. ገናሌ ወንዝ ሐ. ናይል ወንዝ

ለ. የአዋሽ ወንዝ መ. የዋቢ ሸበሌ ወንዝ

25.ከሚከተሉት ውስጥ ቅጠል አርጋፊ የሆነው እፅዋት የቱ ነው?

ሀ. ወይራ

ሐ. ሾላ

ለ. ዝግባ

መ. ቁልቋል

26.ከምድር ወገብ በስተደቡብ የሚገኘው የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ዝናብ የሚያገኙበት ወራት መቼ ነው?

ሀ.በጥቅምትና ሚያዚያ

ሐ. ከሰኔ እስከ መስከረም

ለ. ከታህሳስ እስከ የካቲት

መ. ከሰኔ እስከ ነሃሴ

27.በታንዛኒያና በማዳጋስካር ባሉ የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት በስፋት የሚገኘው የአየር ንብረት ክልል?

ሀ. የሣር ምድር ሞቃታማ የአየር ንብረት ክልል

ሐ. የደጋ የአየር ንብረት ክልል

ለ. የበረሃ የአየር ንበረት ክልል

መ. የሐሩር ሞቃታማ የአየር ንብረት ክልል

28.በተወሰነ መልክዓ ምድር ክልል ውስጥ የሚገኝ የህዝብ ቁጥር የሚጨምርበት ወይም የሚቀንስበት መጠን ማሳያ ምን ተብሎ ይጠራል?

ሀ. የህዝብ  እድገት ምጣኔ

ሐ. የህዝብ  ብዛት

ለ. የህዝብ ስርጭት

መ. የፆታና የዕድሜ ቅንብር

29.በአክሱም ዘመነ መንግስት ጥንታዊ አክሱማውያን የፈጠሩት ፊደላት ምን ይባላል?

ሀ. የኩሽ ፊደላት

ሐ. የአሞቲክ ፊደላት

ለ. የሳባዊያን ፊደላት

መ. የናይሎ ሣህራ ቋንቋ ፊደላት

30.ከምስራቅ አፍሪካ ሃገራት ዝቅተኛ የህዝብ ቁጥር ያላት ሃገር ማን ትባላለች?

ሀ. ጅቡቲ

ሐ. ኢትዮጲያ

ለ. ኤርትራ

መ. ሲሼልስ

31.ከሚከተሉት ውስጥ መንፈሳዊ ቅርስ ***ያልሆነው*** የቱ ነው?

ሀ. የጥምቀት በዓል

ሐ. የመስቀል በዓል

ለ. የአክሱም ሃውልት

መ. የአሸንዳ በዓል

32.በጥንታዊ የሜሮይ ህዝብ የምጣኔ ሀብት መሰረት በምን ላይ የተመሰረተ ነበር?

ሀ. ወርቅ በማንጠር

ሐ. ነዳጅ በማውጣት

ለ. በብረት ማንጠር

መ. በግብርና ስራ

33.ከ60 ዓመት በኂላ ከሮም የተመለሰው የአክሱም ሃውልት ቁመት ስንት ሜትር ነው?

ሀ. 33

ሐ. 204.6

ለ. 24.6

መ. 34

34.የልብ ምትን የሚያፋጥን ፣ የደም ግፊትን የሚጨምርና የመተንፈሻ አካልን የሚያዛባ አደንዛዥ እፅ የቱ ነው?

ሀ. ትንባሆ

ሐ. ሲጋራ

ለ. አልኮል

መ. ጫት

35.የሐረር ግንብ የተሰራበት ዋናውምክንያት ምነድን ነው?

ሀ. የሐረርን ከተማ ነዋሪዎች ከወራሪዎች ለመጠበቅ ሐ. ለሙዚየም

ለ. ለቱሪስት መስህብ መ. የሥነ- ሕንፃ ጥበብ ለማሳየት

36. ጥሬ ሀብትን ዘመናዊ የማምረቻ መሠሪያዎችን በመጠቀም ለተጠቃሚዎች የሚሆን ምርት የሚያመርት ተቋም ምን ተብሎ ይጠራል?

ሀ. ግበርና ሐ. ኢንዱስትሪ

ለ. ንግድ መ. ቴክኖሎጂ

37.ከሚከተሉት ውስጥ ለኤች አይ ቪ ኤድስ መተላለፊያ መንገድ ***የሆነው*** የቱ ነው?

ሀ. ልቅ የሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሐ. በጋራ ሽንትቤት መጠቀም

ለ. አብሮ መመገብ መ. አብሮ መኖር

38.ከሚከተሉት ውስጥ ከ"መ" ሕጎች መካከል መታቀብ የሚያሳየው የቱን ነው

ሀ. ከጋብቻ በፊት ምንም ዓይነት የግብረ ስጋ ግንኙነት አለማድረግ

ለ. በኮንደም መጠቀም

ሐ. አንድ ወንድ ለአንድ ሴት

መ. ሀኪምቤት በመሄድ መመርመር

39.ከሚከተሉት ውስጥ የምክር አገልግሎት አላማና ተግበር ***ያልሆነው*** የትኛው ነው?

ሀ.የተዛባ አመለካከትን መለወጥ

ለ. ችግር በሚከሰትበት ጊዜ ድጋፍ መስጠት

ሐ. ግለሠቦች በጤና ደህንነት አግባብነት ያላቸው ተፅእኖ እንዲቋቋሙ ማድረግ

መ. ከተለያዩ ግለሰቦች የሚሰነዘሩ ችግሮችን እንዳይቋቋሙ ማድረግ

40. በአልኮል ውስጥ የሚገኝ ሱስ አምጪ ኬሚካል ***የሆነው*** የቱ ነው፡፡

ሀ. ኢታኖል ሐ. ካቴኒን

ለ. ኒኮቲን መ. ኮኬይን